# ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞክራሲያ ቅፅ 40 ቁ. 4 ጥር 2007 ዓ.ም.

## ግልጽነትና ጥራት ያለው
## የኅብረት ፖሊሲ መኖር ለትግሉ ወሳኝ ነው!

ከዚህ ቀደም በኅብረት ጥያቄ ላይ ብዙ ተብሏል። ስለ ኅብረት ፖሊሲ ሲገለፅ በርካታዎች በድርጅቶች መካከል የሚደረግ መተባበር ብቻ ይመስላቸዋል። ይህ ግን አንዱ ገጽታ ሲሆን ድርጅቶች በራሳቸው የተለያዩ ምክንያቶች ለመተባበር በማይችሉበት ሁናቴ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ሠራተኛው፣ ገበሬው፣ አስተማሪውና ተማሪው፣ ሴቶች፣ የእድር ተቋማት፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ ነጋዴዎች፣ አርብቶ አደሮች፣ ዘላኖች፣ ወዘተ... መሠረታዊ ጥቅማቸውንና ፍላጎታቸውን መሠረት አድርጎ በመቀስቀስ፣ በማደራጀትና አደራጅቶም በማስተባበር የትግል አንድነት ፈጥሮ መታገል ሊያልፉት የማይችሉት ወሳኝ የትግል እንቅስቃሴ ነው። እንዲያውም ተመክሮ እንደሚያመላክተው ይህ ገፅታው ለታጋይ ድርጅቶች መተባበር ወሳኝ እንደሆነ ነው። ስለሆነም ሁለቱን የትብብር ገፅታዎች መተተንተንና ግልፅ ማድረግ በርዕሱ የጠራ ግንዛቤ ለማግኘት የሚረዳ ነው።

በዋናነት የኅብረት ግምባርን ንድፈ ሃሳባዊ ይዘት ከማብራራት ጀምሮ በአንድ ወይም በሌላ ወቅት ተፈጥረው የነበሩ የኅብረት እንቅስቃሴዎችን በመገምገም ሰፊ ማብራሪያና ትችት ተሰጥቶበታል። በእርግጥም ከዚህ በፊት በተለያዩ ወቅቶች በብዙ ድካምና ጥረት ለልዩ ልዩ ዓላማ የተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች ያዋቀሯቸው የኅብረትም ሆነ የቅንጅት መዋቅሮች የነበሩ መሆናቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። ከእነዚህ ውስጥ በርካታዎቹ ለዴሞክራሲም ሥርዓት መመሥረትም ሆነ ለአገር አድን ትግሉ ቀላል የማይባሉ አስተዋጽኦዎች አበርክተው አልፈዋል። በአመሠራረትም ሆነ በአሠራር ችግር እንዲሁም ከዓላማ ግልጽነትና ጉድለት የተነሳ በርካታ ድክመቶች፣ ችግሮች ስለነበሩባቸው በኅብረትም ተጠናክረው በመቀጠልም ሆነ ከሚጠበቀው ውጤት አንጻር የሚፈለገው ግብ ላይ ሳይደርሱ ሊከስሙ ችለዋል። እነዚህ የኅብረት ሙከራዎች በኢትዮጵያ ውስጥ መሠረታዊ ለውጥን ለማምጣት በተደረገ የትግል ሂደት ታሪክ ውስጥ ታሪክ ሆነው ያለፉ ናቸው።

ዛሬም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ እየደረሰበት ካለው የግፍና የሰቆቃ ኑሮ ለመላቀቅና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በኢትዮጵያ ዕውን ለማድርግና ለመገንባት፤ ሥልጣን የያዘውን ጎጠኛና አምባገነን ኃይል የማስወገድ ተግባር ገና ያልተገባደደ በመሆኑ ሁኔታው አሁንም ቢሆን ሕዝባዊና በድርጅት የተዋቀሩ አገር

ወዳድ ኃይልን አስተባብሮ መታገልን የሚጋብዝ ሆኖ እናገኘዋለን። ግቡን ሊመታ የሚችል ፍሬያማና ውጤታማ የሆነ ኅብረት መመሥረት ይኖርበታል የሚለውን ጥሪ ስናቀርብ ግን ከዚህ ቀደም የነበሩትን የኅብረትና የትብብር ጥረቶች ጥንካሬያቸውንም ሆነ ድክመቶቻቸውን በጥልቀትና በአንክሮ መመርመር ግድ ይሆናል። ካለፉት ተመክሮዎች መልካም ገጽታዎች ለቅመን በማውጣት ለወደፊቱ የሚታሰቡና የሚታቀዱ የኅብረትና የቅንጅት መዋቅሮች ትምህርትና ምሳሌ እንዲሆናቸውና ትግሉ ከደረሰበት ደረጃ ጋር በማጣጣም ይበልጥ ተጠናክረው ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻላል እንላለን። ጎጅ ሆነው የቆዩትን እጸጾች አንድ በአንድ ለይተን በማውጣት ዳግም ትግሉን የማይቀይዱበትን መስተጋብርና መከላከያ ማዘጋጀት የሚያስፈልግ ይሆናል ብለን እናስባለን። ይህም ሁሉ ሆኖ ግን፣ ኅብረቶች ቅንጅቶችና ሌሎች የትብብር ዓይነቶችም የሚመሠረቱት ልዩ ልዩ ፍላጎቶችና ዓላማዎች ባሏቸው ኃይሎች በመሆኑ በትግሉ ሂደት ውስጥ ከልዩ ልዩ መሰናክሎች ሙሉ በሙሉ የጸዱ ይሆናሉ ማለትም አንደማይሆን ግልጽ ነው። ስለሆነም ቅራኔዎችንና ችግሮችን ምንጊዜም ለይቶ በማውጣትና ምንጫቸውንና ምክንያታቸውን በጥልቅ መርምሮ በአግባቡ እንዲፈቱ በማድረግ ሁሉም በህብረት የቆመበት የጋራ መድረክ መጠበቅ ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘመናት የመኖር ሂደቱ ውስጥ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቹ ማለትም፣ በኤኮኖሚው፣ በማህበራዊው መስክ፣ በችግሩ፣ በደስታና በሃዘኑ ሁሉ አንደወጉና አንደ ባህሉ ጊዜውን ገንዘቡንና ጉልበቱን በአንድ አስተባብሮ ለኑሮው የታገለና በዚህም እርስ በርሱ እየተረዳዳ እየተጠቀመ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ የኖረ ነው ። ዛሬም ቢሆን ኑሮውን በዚሁ መንገድ ቀጥሎበት ይገኛል። የዚህ የሕዝብ የዳበረ የኑሮ ልምድ ማሳያ በሕዝብ ውስጥ ተስፋፍተው ያሉት የአነጋገር ዘይቤዎች ናቸው - " ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ"፣ "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር"፣ "በአንድ እጅ አያጨበጭቡም"፣ "ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሃምሳው ግን ሽታው ነው"፣ ...ወዘተ የሚሉ አነጋገሮች በኅብረተሰቡ ውስጥ ሥር ሰደውና ተስፋፍተው ይነገራሉ። ይህን አንጻራዊ ሰላም በሰፈነበት ሁኔታ ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ በተደጋጋሚ የአገሩን ህልውና በጦር ሊፈታተኑ የሞከሩትን የውጭ ጠላቶች ጥቃት ለመከላከል፣ ከአራቱም ማዕዘናት ተጠራርቶ የጎበዝ አለቃውን መርጦ በአንድ ላይ ሆኖ በመትመም፣ የሚከፈለውን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍሎ ጠላቱን ድባቅ መትቶ ሃገሩን በነፃነት እነሆ እስከዛሬ ማቆየቱን በደሙ የጻፈው ታሪኩ ነው። ያም በመሆኑ ስለ ኅብረት እንቅስቃሴና ጥቅሙ ሕዝቡ ከራሱ በላይ ማንም ነጋሪ አያስፈልገውም ብንል ስህተት አይመስለንም።

ይሁንና በሰላም በመኖር ሂደትም ሆነ፣ በጦርነት ሁኔታ እንዲሁም በፖለቲካው ትግል ውስጥ፣ የኅብረት ጽንሰ ሃሳብ በመሠረቱ አንድ ነው። በሁሉም ሁኔታ ኃይልን፣ ጉልበትን ገንዘብን ጊዜን አስተባብሮ የበለጠ ጉልበትን፣ አቅምን አግኝቶ መንቀሳቀስና መታገልን የሚያካትት የሚል ነው።

ሌላው መጠቀስ ያለበት ቁም ነገር በማናቸውም የኅብረት ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ሂደት ውስጥ ልዩ ልዩ መልካምም ሆኑ ጎጂ ባህርያት መከሰታቸው አይቀሬ መሆኑን ነው። የተለያዩ የኅብረት ጥረቶችና እንቅስቃሴዎች የሚገጥሟቸው ችግሮች ክብደትና ቅለት ግን አጅጉን ይለያያል። ለኤኮኖሚና ለማኅበራዊ ጉዳይ ተብለው በሚደረጉ ትብብሮች ውስጥ ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮችን ባንጻራዊ ክብደቱ በቀለለ ማረቅ የሚቻል ሲሆን በፖለቲካው መስክ ግን ከባድና ውስብስብ ሊሆኑ ይችላሉ። ለዚህም ቀደም ብለው በተፈጠሩት ኅብረቶች፣ ቅንጅቶች፣ ... ወዘተ ውስጥ ያጋጠሙትን ችግሮች ለማረቅ ቀላል እንዳልነበረ ዛሬ ትግላችን ያለበት ተጨባጭ ሁኔታ ቁልጭ አድርጎ አሳይቷል።

እንደሚታወቀው አምባገነኑ የወያኔ ቡድንና ግብረአበሮቹ በሥልጣን ኮርቻ ላይ ተቆናጥጠው ሊቆዩ የቻሉት፤ የአገር ህልውናም ሆነ የሕዝብ ጥቅም የሚያስጠብቁ ፖሊሲዎችና ዓላማ ኖሯቸው አይደለም። ለዚህም ላለፉት ሃያ አራት ዓመታት የወያኔ አጥፊ ፖሊሲ በሁሉም መስክ ያስከተለው ቀውስ ምስክር

ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ይህ አገዛዝ ከሕዝብ ጋር ሆድና ጀርባ ነው። ይህም ዋናውና ከፍተኛው ድክመቱ ነው።

እንደ አንድ ኃይል ሆኖ የተነሳ ሕዝብ ምንም የሚያቆመው ነገር የሌለ መሆኑን በመረዳቱ ትብብርንና አንድነትን አጨናጋፊ የሆኑ የተለያዩ መሰናክሎች ሳይታክት ሲቀይስና ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል። በመሳሪያነት ከተጠቀመባቸው፤ ካገለገሉትና እያገለገሉት ካሉት ውስጥ ሦስቱን ለአብነት ያህል መጥቀስ ይቻላል። እነኝህም የደህንነትና የመከላከያ ኃይሉን በባለቤትነት መቆጣጠሩ፤ ዋና ዋና የሆኑትን የአገሪቱን የኢኮኖሚ አውታሮች በእጁ ማስገባቱና ሕዝባዊ ዓላማን ያነገበ ቁርጠኛነት የተላበሰና የተባበረ ተቃዋሚ ኃይል በወያኔ ተንኮልም ሆነ በድርጅቶች ድክመት እውን ሊሆን አለመቻሉ ናቸው።

የመከላከያና የደህንነት ኃይሉን መቆጣጠሩም ሆነ የአገሪቱን ኤኮኖሚ እንደልቡ ማሽከርከር መቻሉ የወያኔን ጊዜያው እንጂ ዘለቄታዊ ጥንካሬን አያመለክትም። የተባበረ ሕዝባዊ ትግል እውን እንዳይሆን የሚያደርገው ጥረትም በሥልጣን ላይ ለመቆየት ያለውን ጽኑ ፍላጎትና ፍርሃቱን እንጂ ጥንካሬውን አያሳይም። በሌላ በኩል ለኢትዮጵያ ህልውናና ለሕዝቧ ደህንነት እታገላለሁ የሚለው፣ በርካታና ሰፊ፣ ግን የተነጣጠለ እንቅስቃሴ በሚያደርገው ኃይል ውስጥ አንጻራዊና ጊዜያዊ ድክመት ያለ መሆኑ ግልጽ ነው። ቢሆንም ለኅብረት እንቅፋት የሆኑትን ልዩ ልዩ ችግሮች በጥሞና ገምግሞ ማስወገድና ማረም ከተቻለ መጪው ጊዜ ጥንካሬውንና ብሩሁ ተስፋን ነው የሚያሳየው።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ውስጥ የተለያዩ ፍላጎቶችና ዓላማዎች በነበሯቸው ልዩ ልዩ ድርጅቶች ስብስቦችና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች መካከል የወቅቱ የትግል ሁኔታ በሚጠይቀው ጉዳይ ላይ እየተንተራሱ ልዩ ልዩ የመታገያ የጋራ ነጥቦችን መለስተኛ ፕሮግራማቸው አድርገው በጋራና በመተባበር ለመንቀሳቀስ ችለው እንደነበር የሚታወስ ነው።

ራቅ ያሉትን ትተን በፋሽስታዊው ወታደራዊ መንግሥት የ17 ዓመታት የግፍ አገዛዝ መጨረሻ ገደማ ፣ ደርግ የሶቭየት ኅብረት አፍቃሪ መሆኑ አጅጉን ያስቆጣው ክፍል፣ አሜሪካ በርዳታ ስም ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑትን ወያኔና ሻዕቢያን አስተባብሮ ባዘመተበት፣ ብሎም በሰሜኑ አገራችን ይካሄዱ በነበሩ በሁሉም የጦር ግንባሮች አምባገነኑ ወታደራዊ ኃይል እየተቸነፈ መምጣቱና ውድቀቱም አይቀሬ መሆኑ በወቅቱ ግልጽ እየሆነ በመጣበት ሁኔታ፣ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆኑ ኃይሎች ዓላማቸው ግቡን ከመታ በጊዜው ኢትዮጵያን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሊመጣ ይችላል የሚል ስጋት በበርካታ ሀገር ወዳድና ለሕዝብ ቀናኢ በሆኑ እንደ ኢሕአፓ በመሰሉ ኃይሎች ይስተጋባ እንደነበርም የሚታወስ ነው።

የአገሪቱ ሉዓላዊነትም ሆነ የሕዝቡን አንድነት አስመልክቶ አደገኛ ሁኔታ እየተከሰተ መምጣቱን የተረዱ ኢሕአፓና በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ የሚባሉ ሌሎች ኃይላት ብዙ ችግሮችን በተለይም ክዳትን ጉተታንና መጠላለፍን የመሳሰሉ እንቅፋቶች ተቋቁመው፤ ከዚህ ቀደም ለኅብረት ከተደረጉ ጥረቶች በይዘቱም ሆነ በዓይነቱ ለየት ያለ የኢትዮጵያ ዴሞክራስያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢድኃቅ) የተባለ ድርጅት ለመመሥረት ችለው ነበር።

ኢድኃቅ የተመሠረተበትን ዓላማውንና ፕሮግራሙን ሳያዛባ ፋሽስታዊው ወታደራዊ ኃይልንም ሆነ በውጭ ኃይል እርዳታ ወደሥልጣን የመጡትን ፀረ ኢትዮጵያ ኃይላትን ሳይሰለስ ታግሎአል። የሕዝብን የመታገል መንፈስ አነሳስቶና አደራጅቶ ትግሉ በቀጣይነት እንዲጓዝም አስችሏል። ሁኔታዎች ተለውጠው በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ባሉ የተለያዩ ድርጅቶች አማካይነት ሰፋ ያለ ኅብረት ሲመሠረት ኢዴኃቅ እንደ ኅብረት አካል መቀጠሉ አላስፈላጊ ስለነበር የኢዴኃቅ ህልውና ሊከስም ችሏል።

በሂደት ምንግዜም አዳዲስ ሁኔታዎች ብቅ ይላሉ፤ ቀደም ብለው ያልታዩ ችግሮችና መልስ የሚሹ ጥያቄዎችም እንዲሁ። ያም በመሆኑ በዚያን ወቅት ግድ ያለው በተለይም የውስጥና የውጭውን ትግል የማስተባበሩ ጥያቄ ስለነበር ለዚህ መልስ ለመስጠት በተለያዩ ወቅትና ቦታ በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል። በርከት ያለ ጊዜና ድካም ፈጅቶ በአገር ውስጥም ከአገር ውጭም በተደራጁ አስራ አምስት የሕብረ-ብሔርና የብሔር ድርጅቶች መካከል የተፈጠረው ኅብረት አንዱ ነበር።

እዚህ ላይ በትግላችን ታሪክ ውስጥ ትብብር አስፈላጊ በሆኑባቸው ወቅቶች የተደረጉና የተሳኩም ጥረቶች የምናነሳው በተለይ ዛሬ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወገኖች እንዲያውቁት ከሚል እንጂ ለኅብረት የተደረጉትን ጥረቶች ሂደትና ታሪክ በሰፊው ለማተት እንዳልሆነ ከወዲሁ አንባቢያን እንዲገነዘቡት ልናሳስብ እንወዳለን።

ባለፉት 24 አመታት የተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይላት መካከል አብሮ በተደጋጋሚ በኅብረት፣ በቅንጅት በትብብር፣ ... ወዘተ ተደራጅተው ያደረጓቸው እንቅስቃሴዎች ትግሉን ወደፊት በማራመድ በኩል ጎላ ያሉ አስተዋጽዖች ማድረጋቸው የማያጠያይቅ ሲሆን በርካታ ድክመቶችና ችግሮችም የነበሩባቸው መሆኑና አሁን ያሉባቸው መሆኑ ግልጽ ነው።

እንደሚታወቀው ዛሬ በአገራችን ምድር አገር እያተራመሰ ያለው የወያኔ አገዛዝ፣ በሁሉም መስክ የተደራጀ ነው። ማለትም የጦር ኃይሉን፣ ደህንነቱን፣ ኢኮኖሚውን ተቆጣጥሮ የሚገኝ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይል ነው። በዚህም ማናቸውንም ያገሪቱን እንቅስቅሴዎች እንዳሻው የሚፈልጥ የሚቆርጥ ኃይል ለመሆኑ ማንም አንግዳ ይሆናል ብለን አንገምትም። ይህ አገዛዝ በሥልጣን ላይ እየቆየ በመጣ ቁጥር፣ በዚያው ለመቆየትም አጅጉን ስለሚሻ አፈናውና ጭፍጨፋው እየጨመረ አንጂ እየቀነሰ አይሄድም። ይህ እንዲሆን ደግሞ ሳያሰልስ ይሠራል። ግፈኛውን አገዛዝ የሚቃወመውን ኃይል ሁሉ ማናቸውንም እርምጃዎች በመውሰድ በቀጥጥር ስር ለማዋል ከፍተኛ ጭካኔ የተሞላበትን ሳይቀር ይወስዳል። ይህን ዓይነቱን እርምጃ አንደልቡ ለመውሰድ ምቹ ሁኔታ ከፈጠሩለት መካከል አንዱና ዋነኛው የተቃውሞ እንቅስቃሴዎቹ በተናጠል መደረጋቸው ነው። በኅብረት ተደራጅቶ ለመታገል አለመቻሉ አምባገነኑን የወያኔ አገዛዝ ሲጠቅም የሕዝቡን ትግል ግን ክፉኛ ጎድቷል። ይህ ትግሉን ለማጠናከር የጎደለው ዓብይ ጉዳይ ህይወት እስካልሰጠነው ድረስ፣ ወያኔ የግፍ አገዛዙን ማለትም ማሰሩን፤ ስየል ማውረዱን፣ መግደሉን፣ ... ወዘተ በመቀጠልና በማስፋፋት እድሜውን ያራዝምበታል።

አዎ ሕዝቡ ከዚህ ቀደም በወያኔ ላይ ቆርጦ በተነሳ ጊዜ፤ እንመራሃለን ብለው የተነሱ አንዳንድ ቡድኖች በቀውጢ ጊዜ ቃላቸውን ሳይጠብቁ በመከዳታቸው ምክንያት ክፉኛ ያዘነና እምነት ያጣ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም፣ በተናጠል የሚደረግ ትግል ሊያበረክት የሚችለው ውሱን አስተዋጽዖ መሆኑን በግምት በማስገባት በኅብረት በመቀናጀት በአንድ ላይ ለመታገል ከምንግዜውም በላይ ዝግጁ መሆን አንደሚያስፈልግ ዛሬም አጽንዖት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ይህ የህዝብ ጥያቄ በአራቱም ማዕዘናት እየተስተጋባ መሆኑ የሚታይ ነው። በበኩላችን ጥያቄው ተገቢና ወቅታውም ነው አንላለን።

ካለፉት የኅብረት ተመክሮዎች የምንቀስማቸው ትምህርቶችና የምንወስዳቸው ግንዛቤዎች የወደፊት የኅብረት ጥረቶችን ችግሮች ለማስወገድና ድክመቶችንም ለማረም አስተዋጽኦ ስለሚኖራቸው ግልጽ አድርጎ ማለፉ ጠቀሜታ አለው።

ከላይ የጠቀስናቸው የተለያዩ የኅብረት ጥረቶች በጊዜያቸው ለትግሉ በርካታ አስተዋጽኦችን አበርክተዋል። ሁሉንም እዚህ ላይ መደርደሩ የሚቻል ቢሆንም ዋና ዋና ይሆናሉ ብለን የምንላቸውን ብቻ ማውሳቱን መርጠናል። እነዚህም፡

- የሕዝቡን የትግል ስሜት ለማነሳሳት ችለዋል፣ ሕዝብን አደራጅተው በትግሉ እንዲሰለፍ አድርገዋል፤ ኃይልን፣ ጉልበትን፣ እውቀትንና ገንዘብን በአንድ ላይ አቀናጅተው ለትግሉ እንዲውል አድርገዋል ብሎም እንደ አንድ ኃይልና ድምጽ ሆነው የወያኔን አገዛዝ ገና ከጅምሩ አንስተው ታግለዋል፤ ትግሉም ቀጣይነት ኖሮት እንዲቀጥል አስችለዋል።

- ድርጅቶቹ ያለፈ ቂም በቀል ሳያግዳቸው ለአገር አድኑና ለዴሞክራሲው ትግል ቅድሚያን በመስጠት አብሮ ለመታገልና ለመሥራት ፈቃደኛ ሆነው አብረው ተንቀሳቅሰዋል፣ ይህም በመሆኑ በሕዝብ ዘንድ ልዩ የአንድነት ትግል ስሜት እንዲፈጠር ለማድረግ ችለዋል።

- በአገርም ውስጥ ሆነ በውጭ ይንቀሳቀሱ በነበሩ የተቃዋሚ ኃይሎች መካከል መልካም የትግል አጋርነትና ትብብር እንዲፈጠር ረድተዋል። ይህን በማድረጋቸው በጠላት መንደር መደናገጥን፣ ለሕዝቡ ደግም መነቃቃትንና ተስፋን ሰጥተዋል።

- ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ በተለይም ደግሞ ለኢትዮጵያ ምን ጊዜም የማይተኙት ኃይላት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የሚያስብ፣ የሚታገል፣ መስዋእትነት የሚከፍል፣ የተደራጀ ጠንካራ የተቃዋሚ ኃይል እንዳለ ለማሳወቅ ችለዋል።

- የወያኔውን የከሰረ ፖሊሲ እርቃኑን እንዲቀር ያደረጉ ሲሆን የሕዝብን የትግል መንፈስ በማነሳሳት ድፍረትን እንዲጎናጽፍና ሁኔታው ከተመቻቸ ሕዝቡ ወያኔን በሕዝባዊ ምርጫና በድምፁ ለማስወገድ የሚችልበትን ሁኔታ በማሳየት የተመክሮ ባለፀጋ እንዲሆን አድርገዋል።

ከላይ የተጠቀሱት ከዚህ ቀደም ተፈጥረው የነበሩት የኅብረት አካላት ለትግሉ ያበረከቱትት መልካም ቱርፋቶቹ ሲሆኑ በተለያዩ ወቅቶች የተፈጠሩት የቅንጅት ሆነ የኅብረት አካላት በምሥረታቸው ወቅት ሆነ በትግላቸው ሂደት ከድክመቶችና ከችግሮች ነፃ እንዳልነበሩ ግልጽ ነው። ለአብነት ያህል አንዳንዶችን ማንሳት ይጠቅማል ብለን እናስባለን።

- የተለያዩ ፍላጎቶችና ዓላማዎች ባሏቸው ድርጅቶች መካከል ሁሉን ሊያስተባብር የሚችል አካል መፍጠር በራሱ አንዱ ከባድ ችግር የነበረ መሆኑ፤
- በአባል ድርጅቶች መካከል የልምድና የአመለካከት ልዩነት መኖሩ፤
- በድርጅቶች መካከል መጠራጠርና ያለመተማመን ሁኔታ መፈጠሩ፤
- በጠላት ላይ ሊኖር የሚገባው ግልጽነት የተለያየ መሆኑ፣ ወያኔን እንደ ጠላትና እንደ ትግሉ ዒላማ አድርጎ መውሰዱ ላይ ቁርጠኝነት መጉደሉ፤
- በኅብረ-ብሔርና በብሔረሰብ አኳያ በተደራጁ ድርጅቶች መካከል ያለውን መሠረታዊ ችግር በተገቢው መንገድ ለማረቅና አብሮ ሊያሠራ የሚችል የአሠራር ዘዴ ለመፍጠር አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱ፤

- አስካሁንም ድረስ መፍትሄ ያልተገኘለት ጽንፈኛ አቋም የሚያቀነቅኑ ኃይላት መኖራቸው፤
- አንዳንዶቹ ድርጅቶች ለጠላት ልዩ ልዩ የመሳቢያ ወጥመዶች ሆነው መገኘታቸው፤ ለሰርጎ ገቦች ሙከራ አመቺ ሆነው መገኘታቸው፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ድክመቶቹንና ችግሮቹን ለማስወገድ ባለመቻሉ በሕዝቡ ስሜት ላይ ቅሬታዎችን ማሳደራቸው ግልጽ ነው።

አነዚህን ድክመቶችና ችግሮች በሚገባ አስተውለን ለወደፊቱ ዘላቂ መፍትሔዎችን ለማግኘት ብዙ መጣርና መድከም ይጠበቅብናል።

ካሁን በፊት ለሕዝብ ይፋ በሆኑ የዴሞክራሲያ እትሞች እንደተጠቀሰው "ህብረት ስንል ብዙዉን ጊዜ ክብደት ያልተሰጠው ሐቅ ግን የኅብረት ፖሊሲ፣ አቋምና ፖለቲካን በኅብረተሰቡ ዘንድ እውን ማድረግን የሚመለከት በመሆኑ በሰፋት ተብራርቷል። ድር ቢያብር አንበሳ ያስር የተባለውን ስንቀበልም ድሩ ሕዝብ መሆኑን ማወቅና በገቢርም መቀበል አስፈላጊ ነው። የድርጅቶቹ መተባበር የሕዝብን በጋራ አላማና እንቅስቃሴ ዙሪያ መተሳሰርን ሊተካ አይችልም። የኅብረት ግንባር ፖለቲካን በመጀመሪያ ደረጃ በሕዝብ ዘንድ እውን ማድረግ የሚለው መርህ በዋናናት ደረጃ የሚጠቅሳቸው የሚከተሉትን ነው።

ሀ. ሰፊውን የሕዝብ ቁጥር ሊያሰባስብ የሚችል አቋምና መፈክሮችን ይዞ ሕዝብን ማደራጀትና ለትግል ማሳተፍ፡

ለ. ኅብረትን ከታች ወደ ላይ ማለትም ሕዝብን (የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ከሠራተኛ፡ ገበሬ፣ አርብቶ አደር፣ ተማሪና አስተማሪ፣ የመንግሥት ሠራተኛ፣ ነጋዴዎች፡ የሴቶች ማኅበር፡ በየሰፈሩና በቀበሌ ደረጃ የተቋቋሙ የእቁብ እድሮች፡ ሌሎች የሲቪክና የሙያ ማህበራት በራሳቸው ፍላጎትና ጥቅም ላይ የተመሰረተ ሙሉ ተሳትፏቸውን ማጠናከር አስፈላጊ ነው።

ይህም የሚያመለክተው ድርጅቶች ያውም ከማኅተምና የተወሰኑ አመራር አባሎች ውጪ አባልም ሚዛንም የሌላቸውን ሰብስቦ ኅብረት ከማለት በፊት በቅድሚያ ሕዝብና ማሰባሰብና የሕዝብ ድርጅቶችን ማጠናከር ይገባል ማለት ነው። እያንዳንዱን የማኅበረሰባዊ ክፍል በነፃ እንዲደራጅ ሊቀሰቅሱትና የትግሉም እምብርት ሊሆን ይገባል ማለት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ኅብረት ኃይል ነው ስለተባለ ብቻ ሁሉንም ማስተባበር የማይቻል ለመሆኑ ያለፉት ተመክሮዎች የሚያመላክቱት ናቸው። ስለሆነም በቅድሚያ ለመተባበር ፍላጎትና ሚዛን የሚደፉ ኃይል ያላቸውን በማስተባበር የፈረጠመ መሆን ከተቻለ ሌሎችን መሳብ የሚያዳግት ሊሆን እንደማይችል የሚታወቅ ነው። ስለሆነም ሁሉ ይተባበር በማለት ብቻ ለኅብረቱ እምብዛም አስተዋፅዖ የሚያደርጉትን ብቻ ሳይሆን ሚናቸው ለሕዝብ ሳይሆን ለባእድ ብሔራዊ ጥቅም የቆሙትን ሳይቀር ማቀፉ በራስ ላይ የመታነቂያ ገመድ ከማጥለቅ ውጪ በምንም አይታይም። ከዚሁ ጋር በተያያዘም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የቆሙና በተፃራሪ ደግሞ ኢትዮጵያዊ አይደለንም ብለው የመገንጠል ዓላማ ከሚያራምዱ ኃይሎች ጋርም ኅብረት መፍጠር የሚሻል አይደለም። ስለሆነም ስለ ኅብረት ሲነሳ ኅብረት ለምን? ከማን? እንዴት? ግልፅነት ባለው መልኩ መልስ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ሲጠቃለል በኢሕአፓ አስተያየት በርካታ ተመክሮዎች በተገኙበት በአሁኑ ወቅት ፀረ ወያኔ የሆኑ ኃይሎችና አገዛዙን በሁለገብ ትግልና ሕዝባዊ አመፅ መወገድ አለበት ብለው ከሚያምኑት ጋር ኃይላቸውን ለማስተባበር ብሎም ድርጅታዊ ቅርፅ ለመስጠት ተቀራርቦ መወያየት ተገቢም አስፈላጊም ነው።

ኢትዮጵያ ዛሬ ከዘጠና ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የሚኖርባት አገር ናት። ልዩ ልዩ ባህልና ወግ ያላቸው የበርካታ ዜጎች መናኸርያ በመሆኗ ውብና የማትጠገብ ውድ አገር ናት። በታሪኳ በተለያየ ወቅት ሉዓላውነቷን ሊደፍሩና ሊያጠቋት ባህር ተሻግረው የመጡባትን የውጭ ጠላቶቿን በተደጋጋሚ በጀግንነት መከታ ህልውናዋንና ነጻነቷን ያስከበረች የኩሩ ዜጎች አገርም ናት። በዚህም የነጻነት ቀንዲልና የመላ ጥቁር ህዝብ መመኪያ የሚለውን መጠሪያ ያተረፈች፣ ለብዙዎች የብሩህ ተስፋ ተምሳሊት ተደርጋ ለመወሰድም የበቃች ነች። ኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶቻችንን ብቻ ለመደቆስ የተዋደቁ ጀግኖች ብቻ ሳይሆኑ፣ ጭቆናና ብዝበዛን፣ ግፍና በደልን ለዘመናት በአገሪቱ ላይ ያሰፈኑትን አገዛዞችና የአምባገነን አስተዳደሮችን አምረው የታገሉና ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉ ዛሬም ድረስ በጽናት ትግሉን የቀጠሉ ጀግኖች የነበሯትና ያሏት፣ የአኩሪ ዜጎች ባለቤትም ናት። አገራችን የሌሎችም ተዘርዝረው የማያልቁ በርካታ መልካም ነገሮች ባለቤት እንደሆነች በተደጋጋሚ የተዘከረላት ናት። ይህ ግን አንዱ ገጽታዋ ብቻ ነው። በሌላው ገጽታዋ ግን ለዘመናት ቀይደዋት በገዟት ጨቋኝና በዝባዥ ገዢዎች የተነሳ የመልካም አስተዳደር እጦት ላስከተሏቸው በርካታ ግፍና በደሎች ሁሉ ሕዝቧ ሰለባ ሆኖ የቆየች፣ ዛሬም ቢሆን ካለፈው ይበልጥ በከፋና በመረረ ሁኔታ ውስጥ በደመ ነፍስ የምትላወስ አገር ናት። የፍትህ ርትዕ እጦት፤ የሕግ መዛባትና ጉድለት፤ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ክፉኛ ጥሰት፤ ሰማይ ሊነካ የደረሰ ሥራ አጥነት፤ ህይወት ቀጣፊ የሆኑ በሽታዎችና ደዌዎች መበራከት፤ የናረ ሙስና መስፈን፤ ብልሹ የትምህርት ሥርዓት መስፋፋት፤ ብቃት ያለው የጤናና የህክምና አገልግሎት አለመኖር፤ ... ወዘተ በጉልህ የሚታይባት አምባገነን የሚያምሳት አገር ስትሆን፣ ሰላምና መረጋጋትን ያጣች፤ በርካታዎች በውስጧ መቆየትን ሳይሆን ውጪውን የሚናፍቁበት አገር ሆናለች። ይህ ቢመረንም ልንውጠው ግድ የሚለን ሐቅ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደጋጋሚ በትከሻው ላይ የሚቆናጠጡ አምባገነኖች የሚያደርሱበትን በደልና ጭቆና ለማስወገድ ሆ ብሎ በትግል ከተመመ ከአርባ ዓመታት በላይ ቢሆነውም፤ በትግሉ የከፈለውም መስዋዕትነት በጣም ከፍ ያለ ቢሆንም ትግሉ ፍሬ አፍርቶ የድል ባለቤት ለመሆን አልቻለም። እናም፣ ዛሬም ለአገር አድን ትግሉና ብሎም ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መመስረት በቁርጠኝነት ታግለው ይህን ድል ለማቅረብ ዝግጁ ለሆኑ ሁሉ አያልፋት ግዳጅ አያመልጡት ሥምሪት ከፊታቸው ተደቅኗል። -- ካለፈው የኅብረት ጥረት መልካሙን ወስዶ ችግሮቹንና ድክመቶቹን አርሞ ጥራትና ቁርጠኝነትን የተላበሰ፣ ኅብረትን የመፍጠር ጉዳይ እንደዋዛ ችላ ሊባል የሚችል አይደለም።

ኢሕአፓ ለዚህ ከፍተኛ ጉዳይ ተገቢውን ክብደት በመስጠት ብዙ ደክሞበታል። ድርጅቱ የኢትዮጵያን የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮች አንድ ወይም የተወሰኑ ኃይላት ብቻቸውን የሚለውጡት እንደማይሆን ካስገነዘበም በርካታ ዓመታት አስቆጥሯል። እንዲያውም በወደፊቷ ኢትዮጵያ የመድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲ መረጋገጥ እንደ ዋና ፖሊሲው የወሰደው በመሆኑ ለተግባራዊነቱም ሳያሰልስ እነሆ እየታገለ ይገኛል። ያም በመሆኑ ባለፉት የትግል ዓመታት ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን የፖለቲካ ኃይሎች ጋር ሊያስማሙ በቻሉ መለስተኛ ፕሮግራሞች ሁሉ የትግል አንድነት ፈጥሮ ታግሏል። ለዚህ ታላቅ ቁም ነገር ሲልም ቂም በቀል ሳያግደው ዝግጁነቱን በተግባር አሳይቷል። ድርጅቱ የተሳተፈባቸው የኅብረት እንቅስቃሴዎች ጠንካራ የትግሉ መሳሪያ ሆነው የኢትዮጵያን ውስብስብና አስቸጋሪ ሁኔታ ለመለወጥ ይበቁ ዘንድ ብዙ ለፍቷል። ብዙ ብዙ መክሮአል፣ ብዙ አድርጓል። ብዙ ታግሏልም። ምንም እንኳን ያለፉት የጋራ ጥረቶች የታለመውን ውጤት ባያስገኙም በኢሕአፓ ግምጋሜ ወደፊት ለሚደረጉ የኅብረት ምስረታ ተሳትፎዎቹ ጥቅማቸው የጎላ ነው የሚላቸውን የቀሰመና የተገነዘበ ሲሆን፣ ድክመቶችና ችግሮች ነበሩ ያላቸውንም ነቅሶ አውጥቶ ለእርምታቸውና ለመወገዳቸው ታግሏል፤ ይታገላልም።

የጦር ኃይሉንና የደህንነት ተቋሙን፣ የኢኮኖሚ አውታሮቹን ተቆጣጥሮ፣ በገንዘብና በመሳሰሉ ጥቅሞች በመደለል የተደራጀን አገዛዝ፣ በተናጠል በሚደረጉ ስብጥርጥር ትግሎች ማስወገድ ቀርቶ ማንገዳገድም

የሚቻል እንዳልሆነ ለማወቅ መላዕክት መሆንን አይጠይቅም። በኛ በኩል ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝቡ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት የሚሆንበት ሁኔታ መረጋገጥ አለበት ባዮች ነን። ያም ይሆን ዘንድ አምረን ታግለናል አሁንም እንታገላለን። የሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነትና ምንጭነት የሚገለጥበት አንዱ መንገድም በአገሪቱ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫን ለማካሄድ የሚያስችሉ መስፈርቶች ሁሉ ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው እንላለን። በአገራችን ዛሬ ይህ እንዳይሆን ትልቅ መሰናክል ሆኖ የሞት የሽረቱን ያህል የሚታገል አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ አለ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ፣ በተናጥል የሚደረጉ የምርጫ ተሳትፎዎች፣ ከዚህ ቀደም ከተሞከሩት የተናጠል የምርጫ ተሳትፎዎች በተለየ ውጤታማ ለመሆናቸው የሚያመልክት ሁኔታ ዛሬ አለ ብሎ ለመናገር አስቸጋሪ ይመስለናል። እንዲያውም እንዲህ ባለው ሁኔታ በምርጫ መሳተፉ ጥቅሙ ለወያኔ አገዛዝ ከመሆን በቀር ለትግሉ የረባ ፍሬ ያመጣል ብሎ መጠበቅ ያለፈውን ታሪክ መርሳትና ስህተትንም መድገም ይሆናል። ስለሆነም ህዝብ የሥልጣኑ ምንጭና ባለቤት ይሆን ዘንድ ብሎም በምድሪቱ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በየደረጃው እንዲደረግ የሚያስችል አካባቢ እንዲፈጠር፣ አስቀድሞ ይህ እንዳይሆን መሰናክል ሆኖ ያለው የወያኔ አገዛዝ መሆኑ ላይ ጥራትና ግልጽነት ኖሮ፤ ወያኔን ማስወገዱ ላይ ቁርጠኝነትን ተላብሶ መገኘትን የግድ ይላል። ይህን ሐቅ የምንጋራ ሁሉ የየራሳችንን ጣጣ ፈንጣጣ ወደ ጎን ትተን በአንድነትና በጋራ ለመታገል በቁርጠኝነት ከተነሳን ብሎም እንደ አንድ አካል የትግሉ ማዕከል በመሆን ሕዝቡን ከዳር እስከዳር ልናደራጀው፣ ልናነሳሳው፣ ልናታግለውና አቅጣጫ ልንሰጠው ከቻልን ዛሬ አጥብቆ እየጠየቀ ላለው የማበርና ትግሉን የማስተባበር ጥያቄ መልስ አግኝቷል ለማለት እንደፍራለን።

ኢሕአፓ በተለያዩ ወቅቶች በዚህ በኅብረት ጥያቄ ላይ ያለውን ፖሊሲ ሳይታክት በሁሉም የመገናኛ ዘዴዎች ለሕዝብ ሲያቀርብ ቆይቷል። አልደራደርባቸውም የሚላቸውን አቋሞቹን ማለትም፣ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፣ የሕዝቦቿን በአኩልነትና በአንድነት የመኖር፣ የወያኔው አገዛዝ ተወግዶ በሕዝብ የሥልጣን ምንጭነት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እውን የመሆኗን አበክሮ ገልጿል። ዛሬም እነዚህ የጸኑ አቋሞቹ ናቸው። በነዚህ ላይ ጥራቱ፣ ግልጽነቱና ቁርጠኝነቱ ካለ ኢሕአፓ የሚከፈለውን ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን በድጋሚ ይገልጻል። ኅብረት የንቃተ ሕሊና ብስለትና የትግል ውጤት እንደመሆኑ መጠን ለመገንባት የሚፈለገው ዴሞክራሲም የኅብረትና የብስለት ውጤት የሚሆነውም በዚሁ ምክንያት ነው።

የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ ጥራትና ግልጽነትን የተላበሰ የተባበረ ትግል ወሳኝ ነው!